የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥርኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ – ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 66
Addis Ababa 23rd August, 2004

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፱/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ/ማሻሻያ/ ደንብ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፰፻፺፩

CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 109/2004
Water Works Construction Enterprise Establishment (Amendment) Council of Ministers Regulation.............................................................................Page 2891

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፱/፲፱፻፺፮

## የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ም/ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ /፩/ /ሀ/ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ
ይህ ደንብ "የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ/ማሻሻያ/ ደንብ ቁጥር ፩፻፱/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ
የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፶፮/፲፱፻፹፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

፩ አንቀጽ ፫ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፫ ተተክቷል።

"፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን
የውሃ ሀብት ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።"

፪· ከአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ /፪/ በኋላ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫፣ ፬ እና ፭ ተጨምረዋል።

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 109/2004 WATER WORKS CONSTRUCTION ENTERPRISE ESTABLISHMENT (AMENDMENT) COUNCIL OF MINISTERS REGULATION*

This Regulation is issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 /1/ /a/ of the Piblic Enterprises Establishement Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*
This Regulation may be cited as the "Water Works Construction Enterprise Establishment (Amendment) Council of Ministers Regulation No. 109/2004".

2. *Amendment*
The Water Works Construction Enterprise stablishment Council of Ministers Regulation No. 156/1994 is hereby amended as follows:–

1 Article 3 is hereby deleted and replaced by the following new Article 3:

"3 Supervising Authority
The Ministry of Water Resources shall be the Supervising Authority of the Enterprise."

2. The following new sub-Articles /3/4/and /5/ are added after sub-Article /2/of Article 5.

"፫" የውሃ ሀብትን ለመስኖ እርሻና ተጓዳኝ ሥራዎች ልማት ለማዋል የሚያስችሉ ግድቦችን በባለቤትነት ይሠራል፣ ያስተዳድራል፣ ለግንባታ ያወጣውን ወጪ ከተጠቃሚዎች በመሰብሰብ ገንዘቡን ለተመሳሳይ ልማት ያውላል፣

፬· ቦንድ ያወጣል፣ ይሸጣል፣ በዋስትና ያስይዛል፣

፭· በተጓዳኝ ለሥራው የሚያስፈልጉትን የተለያዩ ቧንቧዎችን ሊያመርትና ሊሸጥ ይችላል፣"

፫ አንቀጽ ፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

"፮· ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር 3,709,180,000 (ሦስት ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠኝ ሚሊየን አንድ መቶ ሰማንያ ሺ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 205,412,000 (ሁለት መቶ አምስት ሚሊየን አራት መቶ አሥራ ሁለት ሺ ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።"

ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

"3. construct its own dams pertaining to water resource developmant for irrigation and other related development purpose and administer the same; and collect the investment cost from the beneficiaries of such dam; and invest the money on other similar development;

4. issue, sell and pledge bonds;

5. manufacture and sell different kind of pipes necessary for its activities."

3 Article 6 is hereby amended as follows:-

"6. Capital

The Authorized Capital of the Enterprise is Birr 3,709,180,000 (three billion seven hundred nine million one hundred eighty thousand birr.) of which Birr 205,412,000 (two hundred five million four hundred twelve thousand birr) is paid up in cash and kind.

3. Effective Date

This Reulation shall come in to force as of the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of August, 2004

Meles Zenawi
Prime Minister of the Federal
Democratic Republic of Ethiopia